07/04/2021

# ምርጫ 2013 በፖለቲካ ፓርቲዎች እይታ

## ጥያቄዎች ከአበራ

1. *ለሁሉም፤* የተራዘመው 6ኛ ብሔራዊ ምርጫ ግንቦት 28 ይካሄዳል። የውድድሩን ሜዳ እንዴት አገኛችሁት?

2. *ለዶክተር መረራ፤* ድርጅትዎ የኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረስ ከምርጫው ራሱን አግልሏል። እርስዎ ራስዎ ሲታገሉለት የኖሩትን በእኩልነት ላይ የተመሰረተች አንዷት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ፣ ከነ ጉድለቶቹም ቢሆን፣ ምናልባትም ብቸኛው ከሆነው ሰላማዊ የምርጫ ጎዳና ድርጅትዎ ራሱን ማግለሉ ሕይወትዎን ሙሉ የታገሉለትን ዓላማ መና አያስቀረውም ወይ?

3. *ለዶክተር አረጋዊ፣* የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ትግራይ ውስጥ ያለውን ሁኔታ እንዴት ይመለከተዋል? የድርጅትዎስ እንቅስቃሴ ምን ይመስላል።

4. *ለፕሮፌሰር ብርሃኑ* ሆኖ ሌሎቹ የሚጨምሩበት፣ በአንድ በኩል ወደ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ለመሸጋገር የተጀመረው ለውጥ በራሱ በገዢው ፓርቲ የውስጥ ድክመት ጭምር እየተንገዳገደ ባለበት፣ በሌላ በኩል ብሄርና በሄር እንዲጋጭ፣ ሰላም እንዲደፈርስ፣ አገር እንዳይረጋጋ፣ መንግስት እንዲፈርስና ከተቻለም ኢትዮጵያ እንድትበተን ከውስጥና ከውጭ የተቀነባበረ ሴራ እየተሸረበ ባለበት በአሁኑ ወቅት፣ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ሚና እና ኃላፊነት ምን ሊሆን ይገባል ትላላችሁ?

5. *ለሁሉም፣* ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተከሰተ ያለው የዘር ማጽዳት ተግባርና የክልል ድንበር ጠብ በድንገት የተፈጠረ ነገር ሳይሆን የ27 ዓመት ጸረ ኢትዮጵያ የኢሕአድግ ሥራ ውጤት ነው። አንዳንድ የብሄር ድርጅቶችና የክልል መንግስታት የሚያስተጋቧቸው አቋሞች ሁኔታውን ይበልጥ እያባባሰው ነው። ይህንን የኢትዮጵያን የኋሊት ጉዞ እንዴት ማስቆም ይቻላል?

## ጥያቄዎች ከያሬድ

1. ወቅታዊ የሆነውን የአገራችንን የፖለቲካ ድባብ እንዴት ትገልጹታላችሁ? ዛሬ ላይ ያሉ ተጨባጭ ተስፋዎች እና አሳሳቢ ወይም አስፈሪ የምትሏቸ አሳሳቢ ሁኔታዎች ምንድ ናቸው?

2. ከዚህ ግምገማችሁ በመነሳት አገሪቱ ያለችበት ጠቅላላ ሁኔታ ሰላማዊ፣ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ ለማካሄድ አመቺ ነው ወይ? ካልሆነ ለምን? በቀሩት ጊዜት ውስጥ ሊሻሻል ይችላል የሚል ተስፋ እና እድል አለ ብላችው ታስባላችሁ ወይ?

3. የፖለቲካ ፓርቲዎች አገሪቷ ዛሬ የተጋረጡባትን አደጋዎችም ሆነ ቀደም ሲል በተነሱት ውይይቶች ላይ የተጠቀሱ ችግሮችን ለመቅረው ወይም መፍትሔ ለማፈላለግ ምን ተጨባጭ ሥራዎች እየሰራችሁ ነው?

4. በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የሚታየው አለመረጋጋት፣ ግጭት እና ዘር ተኮር ጥቃቶች፣ ጦርነቱን ተከትሎ በትግራይ የተከሰተው ቀውስ በቀጣዩ ምርጫ ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ እንዴት ትገመግሙታላችሁ?

5. በምርጫ ዙሪያ የሚነሱ ቅራኔዎችን ወይም ቅሬታዎችን በቀላሉ እና በአግባቡ ለመፍታት የሚያስችል አሠራር ተዘርግቷል ወይ? ምን ምን? ከሌለስ ለምን?

**ጥያቄዎች ከጽጌረዳ**

1. የመጭው ምርጫ ተስፋና እንቅፋት ናቸው ብላችሁ የምትመለከቱትን ዋና ዋና ጉዳዮች በአጭሩ ብትገልጹልን? ከዲሞክራሲ ግንባታ አንጻር ከዚህ ምርጫ የምትጠብቁት ውጤት ምንድን ነው?

2. **የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤትና ምርጫ**

   የምክር ቤቱ የአጭርና የረጅም ጊዜ አላማውና ግቡ ምን ምን ናቸው? የጋራ ስምምነት የተደረሰባቸውንና ልዩነቶች ካሉ፣ ልዩነቶቹ በምን ላይ እንደሆኑ ቢያስረዱን? የምርጫውን ዝግጅት ምክር ቤቱ እንዴት ይገመግመዋል?

3. **ምርጫና በነጻ የመምረጥ መብት**

   የ1948 የተባበሩት መንግስታት የሰባዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 21፣ ማንኛውም ሰው ብቀጥታ ወይም በነጻ በተመረጡ ተወካዮቹ አማክኝነት በሀገሩ የመንግስት አስተዳደር የመካፈል መብት አለው ይልና፣ የህዝብ ፍላጎት የመንግስት ስልጣን መሰረት ይሆናል ይላል።
   አንቀጽ 2፤ ማንኛውም ሰው በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋዋንቋዋ፣ በሃይማኖት፣በፖለቲካ ፣ በብሄረሰብ ወይም ማህበራዊ ምንጭ ወይም ሌላ አይነት አስተሳሰብ ልዩነት ሳይደረግበት የሰባዊ መብቶች ድንጋጌ የመጠቀም መብት አለው ይላል።

   እነዚህን የሰው ልጆች የማይገሰሱ መብቶች በተግባር ለመተርጎም፣ የዲሞክራሲያዊ ተቅዋማት ያስፈልጋሉ። ስለዚህ፣ የሰባዊ መብት መከበር ያለዲሞካርሲ ተቋማት፣ የዲሞክራሲ ተቋዋማት ያለሰብአዊ መበት መከበር ሊኖሩ አይችሉም። የተሳሰሩ ናቸው። አገራችን ዛሬ ባለችበት ሁኔታ፣ ምርጫ አለመካፈል ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መብቶች በከፊልም ቢሆን ስራ ላይ እንዳይውሉ አስተዋጽኦ ማድረግ አይሆንም ወይ?

4. **ብሄራዊ እርቅ ብሄራዊ መግባባት**

   ከአንዳንድ አካባቢዎች፣በተደጋጋሚ ከሚነሱት ጥያቄዎች አንዱ ብሄራዊ እርቅ ወይም ብሄራዊ መግባባት ነው። ከዚህ ድፍን አነጋገር ባሻገር፣ ብሄራዊ መግባባትና እርቅ የሚስፈልጋቸውን ዋና ዋና ጉዳዩች የሚሉዋቸውን በተጨባጭ አንድ ሶስት ምሳሌ ቢሰጡን?

   ለዲሞክራሲ ግንባታ ሂደት የሚያግዙ ብዙ ተቋዋማት ከ2010 ጀምሮ ተመስረተዋል። ከነዚህም ውስጥ **የወሰንና የማንነት ኮሚሽንና የእርቅና የሰላም ኮሚሽን** *ይገኙበታል። በነዚህ ኮሚሽኖችውስጥ የእናንተ ተሳትፎ ወይም አስተዋጽኦ ምንድን ነው? የእናንተ ፓርቲ ለነዚህ ክሚሽኖች፣ የሃገሪቱ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው የምትሉትን ለይታችሁ ከነመፍትሄውዎቹ አቅርባችሁዋል ወይ?*

የወሰንና የማንነት ኮሚሽን፣ ከ28 ዩኒቨርስቲ የተውጣጡ፣ 78 ተመራማሪዎች የተሳተፉበት፣ ማንነትን፣ ወሰንንና አስተዳደርን በትመለከተ ሰፊ ጥናት እንዳደረገና በግንቦት ወር እንድሚያቀርብ አስታውቆአል። ከአጥኒዎቹ ጋር ተገናኝታችሁ ተወያታችሁዋል?

5. **የፖለቲካ ፓርቲ የምርጫ ፕሮግራም**

የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ዋና አላማና ግብም ፣ ምረጡኝ ለሚሉት ህዝብ፣ በተለይም በአለም አቀፉ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ድንጋጌ መሰረት የህዝቡን ኑሮ ለማሻሻል፣ ለችግራቸው መፍትሄ ይሆናል የሚሉትን ፖሊሲ በይፋ ለውይይት ማቅረብ ነው። እነዚህም መብቶች፣ ለአንድ ዜጋ በክበርና በነጻነት ለህልውናው የሚስፈልጉትን መሰረታዊ የሆኑትን እንደ የምግብና ውሃ ዋስትና፣ መኖሪያ ቤት፣ የጤና ግልጋሎትና ትምህርት የሚስፋፋበትን፣ የስራ መስክ የሚዳብርበትንና የመሳሰሉትን የልማት ጥይቄዎች ቢመረጡ እንዴት ስራ ላይ እንድሚያውሉት ማስረዳት ይኖርባቸዋል። በዚህ መሰረት፣ የእናንተ ፖለቲካ ፓርቲ ለመራጭ አማራጭ የምትሉዋቸውን ዋና ዋና ጉዳዮች ብታስረዱን?

**ጥያቄዎች ከገበያው**

**ለሁሉም ተጋባዥ የፓርቲ መሪዎችና ተናጋሪዎች፡**

1. 6ኘው አገራዊ ምርጫ በአገሪቱ የለውጥና የዴሞክራሲ ግምባታ ሂደት የሚኖረው አስተዋጾ፣ በየፓርቲዎቻችሁ እንዴት ይገመገማል?
2. ምርጫው ሰላማዊ እንዲሆን መንግስት ማድረግ ካለበት በተጨማሪ ፓርቲዎቻችሁ በተጨባጭ ምን እያደረጉ ነው?
3. ምርጫውን ሰላማዊ ለማድረግና ውጤቱንም ለመቀበል በአባሎቻችሁና ደጋፊዎቻችሁ ያለው ዝግጁነት ምን ያህል ነው?
4. ኢትዮጵያን ከ6ኛው ምርጫ ማግስት፣ እንዴት ትስሏታላችሁ?

**ለዶክተር መራራ**

1. በምርጫ እንደማይሳታፍ ተቃዋሚ ፓርቲ ለአባሎቻችሁና ደጋፊዎቻችሁ የምታስተላልፉት መልክት መንድን ነው? ምርጫውን በይኮት እንዲያደርጉ፣ ሌላ ፓርቲ እንዲመርጡ ወይስ እራሳቸው እንዲወስኑ?
2. እንደ ኢትዮጵያ ባለ የዴሞክርራሲ ጀማሪ አገር የአንድ በምርጫ የማይሳተፍ ፓርቲ ሚና ምን ይሆናል?

**ጥያቄዎች ከነገደ**

1. አንሳተፍም የሚሉ ድርጅቶች ምንም መከራከሪያዎች ቢያቀርቡም በሃገራችን እስከዛሬ ከተደረጉት ምርጫዎች ዘንድሮው ከሁሉም የነጻና ፍትሃዊ ምርጫዎችን ያሟላ ሂደት መሆኑ የሚካድ አይደለም፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ በኢህአዴግ ስር ምርጫ የተሳተፉት ዶ/ር መረራ ዛሬ አልሳተፍም ሲሉ ካለፈው የባሰ ለዴሞክራሲ የማየመች ሁኔታ አለ ለማለት ነው ወይ?

2. ዶክተር አብይ ሂደቱን አስመልክተው በፓርላሜንት ባደረጉት ንግግር የምርጫውን ሂደት ለማደናቀፍ ዜጎች ደህንነት እንዳይሰማቸውና ወጥተው እንዳይመርጡ በውጭ ሃይሎች የተገዙ ወገኖች በተለይ ዘር ተኮር ግድያዎችን ሊያባብሱ ይችላሉ የሚል ስጋት እንዳለ ተናግረዋል፡፡ ስልዚህ የናንተስግምገማ ምን ይመስላል

3. በዚህ ምርጫ ማንም ሳያስገድደው ከልቡ ለመሳተፍ የሚወጣውን ህዝብ በሂደቱ ውስጥ መሳተፉና በአብዛኛው ህዝብ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የተመረጠ መንግስት ከመጣ፣ በምርጫው የማይሳትፉ

ሃይሎች የሚያደርጉት ትግል እንደ ዱሮው ከጸረ ህዝብ መንግስት ጋር የሚደረግ ትግል አርጎ መውሰድ ይቻላል ወይ??